


# ከጁላይ 11-20/2025 የነበረዉ የአየር ሁኔታ ግምግማ

# እንዲሁም

# ከጁላይ 21-31 እና ከኦገስት 1-10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ 24 ሰዓት ዉስዋ ከ30 ሚ.ሜ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 36.5፣ ኮምቦልቻ 39.6፣ ቢሾፍቱ 41.4፣ 37.7፣ ነቀምት 35.8፣ ሮቤ 40.2፣ አዲስ አበባ 35፣ አይደር 31፣ አይራ 32፣ አማን 61.3፣ አንገር ጉትን 33.2፣ 39.4፣ አርጆ 32.6፣ አየሁ 36፣ አይከል 31.3፣ ብላቴ 32.7፣ ቦሬ 30፣ ቡለን 30፣ 34.5፣ ዳንግላ 31፣ ደብረ ብርሃን 31.6፣ ደብረ ወርቅ 33.1፣ ኢጃጂ 40.2፣ ፉኙንዶ 42፣ ጋምቤላ 30.5፣ ጊዳ አያና 38.1. ጊምቢ 31.3፣ ጉንዶ መስቀል 52.3፣ ሆሳዕና 31፣ ካቺሴ 30.2፣ ማይጨዉ 30፣ ማንኩሽ 46.6፣ ሞጣ 47.9፣ 39.6፣ ኑራ ኤራ 34፣ 60.7፣ ፓዌ 31፣ ሳውላ 34.5፣ ሾላ ገቢያ 50.5፣ ጽጺቃ 30.2፣ አባይ ሸለቆ 32.3፣ አዲ አርቃይ 90፣ 95፣ 90.1፣ 98፣ 105፣ አቃቂ 41፣ አሳሳ 59፣ አታንጎ 36.5፣ 45.3፣ አዋሽ ሸለቆ 32.3፣ ቡልቂ 31.5፣ ቡሬ 30፣ ጨፌ ዶንሳ 67.3፣ ደራ 40.5፣ 35.5፣ 35.5፣ 60፣ 70፣ 55.5፣ እንዳ በጉና 39፣ ፈረስ ቤት 33.7፣ ፊንጫ 57.7፣ ጋሸና 39፣ 106.9፣ 52.5፣ ጊናገረ 38.9፣ ጉብሬ 49.3፣ ጉጉፊቱ 32.4፣ ሃይቅ 33.2፣ ሃሮ 32.1፣50፣ 32.1፣ ሀርዶዮ 48.5. ከሚሴ 30.5 ቅዳሜ ገበያ 46.8፣ 36.7፣ ኩሚ 40፣ ሙጊ 56.4፣ ኦሞ ናዳ 40.4፣ 37.6፣ ኦንጋ 32፣ ሼንዲ 31.5፣ 53.5፣ 32.5፣ ያንፋ 39.7፣ 68፣ 57.5፣ ያዮ 41.3፣ 42.7፣ ይርጋጨፌ 64፣ ዲክሲስ 33.2 እንዲሁም መንደር አስራ አንድ 45፣ 82፣ 42፣ 38 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።


በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁላይ የሁለተኛዉ አስር ቀናት በ70 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስዋ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.5 እስከ 106.9 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ጋሸና፣ አዲ አርቃይ፣ መንድር አስራ አንድ፣ ደራ፣ ያንፋ፣ ጨፌ ዶንሳ፣ ይርጋጨፌ፣ አማን፣ ኑራ ኤራ፣ አሳሳ፣ ሙጊ፣ ሺነዲ፣ ጉንዶ መስቀል፣ ሾላ ገበያ፣ ሀሮ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute




ምስል፡1 ከጁላይ 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው


ባለፉት የጁላይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከልና አሶሳ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ61-473 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን

ባለፉት የጁላይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ አሶሳ፣ ካማሺ፣ መተከልና ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡

በሌላ በኩል በኤሊዳር፣ አይሻ፣ ገዋኔ፣ አዋሽ አርባ፣ ድሬ ዳዋ፣ ጭፍራ፣ ዳሊ ፋጊ፣ ቀበሪዳሀር፣ መተሃራ፣ ጎዴ፣ መተማ፣ ጨፋ፣ ጋምቤላ፣ ፉኚዶ፣ ኑራ ኤራ፣ መኤሶ፣ ባቲ፣ ላሬ፣ ጅግጅጋ፣ ኮምቦልቻ፣ አቦምሳ፣ ማጀቴ፣ ምዕራብ አባያ፣ አቦቦ፣ ስሪንቃ እና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 30.4 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ያለዉ እርጥበት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ እንደነበራቸው የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም የተገኘዉ እርጥበት ከጁን ጀምሮ ለተዘሩና አሁንም በመዘራት ላይ ላሉ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችንና ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ያሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር የጎላ አስተዋፅዖ ነበረዉ። በተጨማሪም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር  አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ለመጥቀሰም ያህል ደቡብ ወሎ ዞን መቅደላ ወረዳ ነፋስ ቀላቅሎ የጣለ ከባድ ዝናብ በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን እንዲሁም በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ስፍራዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት አስከትሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የወንዝ መሙላትና የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፣ በግብርናዉ እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም (ካርታ 4)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት የጁላይወ ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ መረብ ጋሽ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በተለይ በታችኛው ኦሞ ጊቤ እና በመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ መሻሻል ጥሩ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ሆኖም ግን በአንዳምድ አካባቢዎች ለመጥቀስ ያህል በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ዞን ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ የጣለውን ከባድ ዝናብ ተከትሎ የማሽንጋ ወንዝ በመሙላቱ በተከሰተ ጎርፍ በሰው ህወት ላይ ጉዳት አድርሷል። በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛ እና ታችኛው ዋቢ ሸበሌ፣ በጥቂት ታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ዝቅተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም ሁኔታ በተፋሰሶቹ ላይ በቂ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንዳይኖር አድርጓል(ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁላይ ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ሙሉ በሙሉ ያዳርሳል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይስተዋላል። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ18-27 ቀናት ያህል ይዘንባል። በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ60-200ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ6-21 ቀናት ያህል ይዘንባል፡፡ ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁላይ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ30 እስከ 50% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁላይ ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 1)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | የዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ..ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁላይ የሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ30.2 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን ይበልጥ የሚጠናከሩ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን መካከለኛው እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፉ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖራቸዉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሊባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች የዋግ ህምራ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የከፋ፣ ኮንታ፣ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ የእርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ከሐምሌ ጀምሮ ለሚዘሩ ሰብሎች ለማሳ ዝግጅት ለማድረግ<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በእርሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• ውሃ ገብ በሆኑና አካባቢዎች የአፈር መሸርሸርና መታጠብ<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የሸክላማ አፈር ያላቸው ማሳዎች መጨቅየት | • በሚኖረው እርጥበት ዘር መዝራት<br>• ትርፍ ውሃን ከማሳ በማንጣፈፍ ማስወገድ<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ ሁሉም የክልሉ ዞኖች አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፊንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ቀድመው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በእርጥበት መጎዳት | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ |
| የምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የዘር መዝራት<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት መሰብሰብ |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖችች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት መሰብሰብ |

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.6 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የጁላይ ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። እንዲሁም አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ እንዲሁም የወንዞች ከፍታ መጨመር በላይኛው ተፋስስ በሚነሱ ወንዞች በታችኛው ተፋሰሶች ላይ የወንዞች መጥለቅለቅ የማስከተል። በመሆኑም

በወንዝ ዳርቻ እንዲሁም ረግረጋማ የሚኖሩ ማህበረሰብ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡በተጨማሪም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው አደጋ ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ከታች ተዘርዝረዋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ፣ አኮቦ፣ አዋሽ፣ ላይኛው እና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል | • የቅፅበታዊ ጎርፍ ስጋት መጨመር<br>• የወንዞች መሙላት<br>• በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፊ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ወራጅ ውኃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| በአብዛኛው መካከለኛው እና የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ኦጋዴን | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ | • በጎርፍ ሆነ በደለል ስጋት አለ መኖር | • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል<br>• ከጣራ እና ከመሬት ወለል የዝናብ ውሀን በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ እጥረት በሚገጥማቸው አካባቢዎች የውሀ ተደራሽነትን ማረጋገጥ |